የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፲፩ኛ ዓመት ቁጥር ፳፯
አዲስ አበባ – መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 27
Addis Ababa 29th March, 2005

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፭/፲፱፻፺፯ ዓ·ም
ስለውሃ ሀብት አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት
ደንብ ........................................................ ገጽ ፫ሺ፶፯

## CONTENTS

Council of Ministers Regulation No. 115/2005
Ethiopian Water Resources Management
Regulations ........................................... Page 3057

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፭/፲፱፻፺፯
### ስለውሃ ሀብት አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፯/፲፱፻፺፪ አንቀጽ ፴ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፭/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩· በኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፯/፲፱፻፺፪ ለተዘረዘሩት ቃላት የተሰጡት ትርጓሜዎች በተመሳሳይ ሁኔታ በዚህ ደንብ ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፪· "ፖሊሲ" ማለት የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲ ነው።

፫· "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፯/፲፱፻፺፪ ነው።

### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO. 115/2005*
### *ETHIOPIAN WATER RESOURCES MANAGEMENT REGULATIONS*

Thise Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, Proclamation No, 4/1995 and Article 30 of the Ethiopian Water Resources Management Proclamation No. 197/2000.

### PART ONE
### GENERAL

1. *Short Title*

   Thise Regulation may be cited as the "Council of Ministers Ethiopian Water Resources Management Regulations No. 115/2005".

2. *Definitions*

   Unless the context of otherwise, requires in these Regulations:

   1) Definition given for the terms specified under the Ethiopian Water Resources Management Proclamation No.197/2000, shall have also effect in thise Regulations.
   2) "Policy" means the Ethiopian Water Resources Management Policy;
   3) "Proclamation" means the Ethiopian Water Resources Management Proclamation No. 197/2000;

፬· "የውሃ ጉድጓድ" ማለት በእጅ ከሚቆፈሩ የውሃ ጉድጓዶች በስተቀር ለተለያዩ አገልግሎቶች የተለያዩ መሣሪያዎችን (ሪግ) በመጠቀም የከርሰ ምድር ውሃ አመንጪ ወይም አስተላላፊ አካሎችን በመዝለቅ የሚቆፈር ጉድጓድ ነው።

፭· "የውሃ አቅርቦት ጉድጓድ" ማለት ለመጠጥ ፣ ለእርሻም ሆነ ለኢንዱስትሪ ወይም ለሌሎች ግልጋሎቶች የሚቆፈር ጉድጓድ ነው።

፮· "የውሃ አጠቃቀም" ማለት ውሃን ለመጠጥ፣ ለመስኖ/ለእርሻ/፣ ለኢንዱስትሪ ፣ ለኃይል ምንጭነት፣ ለትራንስፖርት፣ ለቱሪዝም፣ ለእንስሳት እርባታ ፣ ለዓሣ ማስገር ወይም ለሌሎች ግልጋሎቶች መጠቀም ማለት ነው።

፯· "ተቆጣጣሪ አካል" ማለት የውሃ ሀብት ሚኒስቴር ወይም በአዋጁ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት ከሚኒስቴሩ ውክልና የተሰጠው አካል ነው።

## ክፍል ሁለት
## የውሃ ሀብት አጠቃቀም

፫· የፈቃድ ማመልከቻ

በአዋጁ አንቀጽ ፲፫ ድንጋጌ መሠረት በውሃ ሀብት ለመጠቀም ፈቃድ እንዲሰጥ ለተቆጣጣሪ አካል የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፣

ሀ) የአመልካቹን ስምና ቋሚ አድራሻ፣
ለ) የውሃ ሀብቱ የሚገኝበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ክልል ልዩ ቦታ፣
ሐ) የውሃ ሀብቱ ጥቅም ላይ እንዲውል የታቀደበት የግልጋሎት ዓይነት፣
መ) በየወሩና በየዓመቱ ሊወሰድ የታቀደው የውሃ መጠን፣
ሠ) በምን ዓይነት ዘዴ ወይም ሁኔታ ውሃን ወስዶ ለመጠቀም እንደታቀደ፣
ረ) እንደአግባቡ የኢንቨስትመንት ሠርቲፊኬት፣
ሰ) ተቆጣጣሪው አካል ያስፈልጋሉ ብሎ የሚጠይቃቸው ዝርዝር ጥናቶችና ካርታዎች፣

፬· የተቆጣጣሪው አካል ተግባራት

፩· በውሃ ሀብት የመጠቀም ፈቃድን የሚመለከት ማመልከቻ ተቆጣጣሪው አካል ሲደርሰው ማመልከቻው የደረሰው መሆኑን ወዲያውኑ ለአመልካቹ በጽሑፍ ያረጋግጣል፣

፪· ተቆጣጣሪው አካል በውሃ ሀብት ለመጠቀም ፈቃድ ለማግኘት የቀረበ ማመልከቻን በሚያይበት ጊዜ፣ በአመልካቹ የቀረበው በውሃ ሀብት የመጠቀም ጥያቄ ፖሊሲውን፣ የተፋሰስ ማስተር ፕላኖችን፣ አዋጁን፣ ይህ ደንብ እና መመሪያዎችን መሠረት ያደረገ መሆኑን ያረጋግጣል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ተቆጣጣሪው አካል የቀረበውን ማመልከቻ አስመልክቶ የሚሰጠውን ውሣኔ ለአመልካቹ ማስታወቅ አለበት።

፬· ተቆጣጣሪው አካል በውሃ ሀብት የመጠቀም ማመልከቻን አስመልክቶ የሰጠውን ውሣኔ፣ በአዋጁ አንቀጽ ፲/፪ መሠረት መዝግቦ መያዝ አለበት።

፭· ጥቅም ላይ የዋለ ውሃን ስለመልቀቅ

የአዋጁ አንቀጽ ፲፫/፪/ እና የዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ እንደተጠበቀ ሆነው በውሃ የመጠቀም ፈቃድ ጥቅም ላይ የዋለ ውሃን በአግባቡ አክሞ ወደ ውሃ ሀብት የመልቀቅ መብትን ጨምሮ ሊሰጥ ይችላል።

4) "Water Well" means any well, excepting hand-dug wells, drilled, for various purposes, by means of various equipment (rigs) in order to penetrate and reach underground permeable beds containing or transmitting water;

5) "Water Supply Well" means a well drilled to supply water for drinking, agriculture, industry or other uses.

6) "Water Use" means the use of water for drinking, irrigation, industry, power generation, transport, animal husbandry, fishing, mining and uses of water for other purposes.

7) "Supervising Body" means the Ministry of Water Resources or any organ delegated by the Ministry pursuant to Article 8(c) of the Proclamation.

## PART TWO
## WATER RESOURCES UTILIZARION

3. *Application for Permit*

An application to be submitted to the Supervising Body for a water use permit, pursuant to Article 13 of the Proclamation, shall contain the following information;

(a) the name and permanent address of the applicant;
(b) the location of the water resources and the intended place of use;
(c) the intended use of the water resources;
(d) the volume of water required monthly and annually;
(e) the intended method and manner of use of the water resources;
(f) where appropriate, investment certificate;
(g) feasibility studies and maps reasonably required by the Supervising Body.

4. *Duties of Supervising Body*

1) On receipt of an application for a permit to use water, the Supervising Body shall notify the same to the applicant in writing.;

2) Without prejudice to Article 14(1) of the Proclamation, in dealing with an application for a water use permit, the Supervising Body shall ensure that the application is in line with the Policy, the Rover Basin Master Plans, the Proclamation, thise Regulations and Directives.

3) Subject to Sub-Article (2) of this Article the Supervising Body shall notify in writing the applicant of its decision regarding the application according to Article 14(1)and (3) of the Proclamation.

4) The Supervising Body shall register all decisions given with respect to an application for a permit to use water, according to Article 10(2) of the Proclamation.

5) *Discharge of Water After Use*

Without prejudice to Article 13(2) of the Proclamation and Article 11 of thise Regulations a water use permit may authorize the discharge of treated waste water into a water resources.

፮· <u>በውሃ የመጠቀም ፈቃድን ስለመሰረዝ፣ ማገድ፣ ማስተላለፍና መለወጥ</u>

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፲፯ መሠረት በውሃ የመጠቀም ፈቃድ በተቆጣጣሪው አካል በሙሉ ወይም በከፊል ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈቃዱን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያሳግዱ የሚችሉ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) በፈቃዱ ውስጥ የተጠቀሱትን ገደቦችና ግዴታዎች አለመጠበቅ ወይም አለማክበር፣

ለ) ከተፈቀደ አገልግሎት ውጪ በውሃ መጠቀም፣

ሐ) የውሃ ግልጋሎት ዋጋ ማስታወቂያ በደረሰ በስድሳ (፷) ቀናት ውስጥ የውሃ ግልጋሎት ዋጋ ያለመ ክፈል።

መ) የውሃ ሀብቱ ጊዜያዊ በሆነ መልክ እየመነመነ መሆኑን ተቆጣጣሪው አካል ሲደርስበት፣

ሠ) የውሃ ጥራት ደረጃዎችን አለመጠበቅ፣

፫· ተቆጣጣሪው አካል ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዝ ይችላል፣

ሀ) በፈቃድ ውስጥ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ በተፈቀደው ውሃ በገዛ ፈቃድ ሳይጠቀሙ መቅረት፣

ለ) ተቆጣጣሪው አካል ሳይፈቀድ በውሃ የመጠቀም ፈቃድን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ።

ሐ) ባለፈቃዱ ፈቃዱን ሊያገኝ የቻለው የሀሰት ማስረጃ በመስጠት መሆኑ በተቆጣጣሪው አካል ሲረጋገጥ፣

መ) የውሃ ሀብቱ ዘለቄታዊ በሆነ መልክ እየመነመነ መሆኑን ሲያረጋግጥ፣

ሠ) የባለፈቃዱ የውሃ አጠቃቀም በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፱/፲፱፻፺፬ በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሠረት በአካባቢው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ ሲረጋገጥ፣

፬· ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ከተዘረ ዘሩት ምክንያቶች ማናቸውም መፈጸማቸውን ሲያረጋግጥ ለፈቃድ ያገኙ በሚሰጠው የአሥራ አምስት ቀናት የጽሑፍ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ውስጥ ባለፈቃዱ ሁኔታውን በማስረጃ ካላስተባበለ በስተቀር ፈቃዱን በከፊል ወይም በሙሉ ሊያግድ ይችላል።

፭· ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ /ሐ/ ከተመለከተው ምክንያት በስተቀር በንዑስ አንቀጽ ፫ /ሀ/ /ለ/ /መ/ ወይም /ሠ/ የተዘረዘሩት ምክንያቶች መፈጸማ ቸውን ሲያረጋግጥ ለፈቃድ ያገኙ በሚሰጠው የአሥራ አምስት ቀናት የጽሑፍ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ውስጥ ባለፈቃዱ ሁኔታውን በማስረጃ ካላስተባበለ በስተቀር ፈቃዱን ሊሰርዝ ይችላል።

፮· በውሃ የመጠቀም ፈቃድ እንዲለወጥለት ወይም በሙሉ ወይም በከፊል እንዲተላለፍለት ፈቃድ ያገኙ ለተቆጣ ጣሪው አካል ሊያመለክት ይችላል። ማመልከቻውም በውሃ የመጠቀም ፈቃዱ እንዲለወጥ ወይም እንዲተላለፍ የተፈለገበትን ምክንያትና መለወጡን ወይም መተላለፉን ለመፈጸም እንዲሟሉ የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎችና ገደቦች መግለጽ አለበት።

6. *Termination, Suspension, Transfer or Variation of a Water Use Permit*

1) A water use permit may be terminated or suspended by the Supervising Body in whole or in part as per Article 17 of the Proclamation.

2) A permit may be suspended in whole or in part according to sub-Article (1) of this Article due to the following reasons:

(a) a failure to comply with the terms and conditions prescribed in the permit;

(b) a use of water for purposes not authorized;

(c) a failure to pay the required water charges within sixty (60) days following a written notification;

(d) a finding by the Supervising Body that the water resources Involved is being temporatily depleted;

(e) a failure to keep a water quality standard.

3) The Supervising Body may terminate a permit due to the following reasons:-

(a) a voluntary failure, in excess of the period fixed in the permitee, to utilise the water represented by the permit;

(b) an undertaking to transfer the permit without the authorization of the Supervising Body;

(c) a discovery by the Supervising Body, that the permit has obtained the permit by giving false evidence;

(d) a finding that the water resources involved is being permanently depleted;

(e) a finding that the usage of the water resources causes a negative impact on the envirionment as per the Provisions of Envionmental Impact Assessment Proclamation No, 299/2002.

4) The supervisiong Body may suspend a permit whole or in part as case may be giving 15 days prior warning in writing when it ascertain that any of the reasons stated under sub-article (2) of this Article are committed; if the permit holder fails to refute by evidence about the facts stated in the prior warning within the given 15 days.

5) The Supervising Body may terminate a permit, except for the reason stated under sub-article 3(c) of of this Article, when it ascertain that the reasons stated under sub-article 3(a), (b) or (e) is committed by giving 15 days prior warning in writing, if the permit holder fails to refute by evidence about the facts stated in the prior warning within the given 15 days.

6) The holder of a water use permit may apply to the Supervising Body to vary or to transfer the permit in whole or in part. In such situation the application shall state the reasons for the variation or transfer and it shall indicate the terms and conditions where under the variation or transfer is to be effected.

፯· ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ መሠረት የተወሰደ ማንኛውንም እርምጃ በውሃ የመጠቀም ፈቃድ መዝገብ ውስጥ እንዲመዘገብ ያደርጋል።

## ክፍል ሦስት
## የውሃ ሥራ ፈቃድ

፯· *ማመልከቻዎችና አፈጻጸማቸው*

፩· የውሃ ሥራዎች የመሥራት፣ የማደስ ወይም የመለወጥ ፈቃድን የሚመለከት ማመልከቻ ለተቆጣጣሪው አካል መቅረብ አለበት።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ የውሃ ሥራውን ዲዛይን፣ ደህንነትና አደጋ አልባነትን ያካተተ ሙሉ ዝርዝር ጥናት የያዘ መሆን አለበት።

፫· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውሃ ሥራዎችን ለመሥራት ለማደስ ወይም ለመለወጥ በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ የዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ ፩፣ ፪፣ ፫፣ እና ፬ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፰· *ፈቃዱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜና የሚራዘምበት ሁኔታ*

፩· የውሃ ሥራዎች ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የውሃ ሥራውን የአገልግሎት ዘመን ታሳቢ በማድረግ በተቆጣጣሪው አካል ይወሰናል።

፪· የውሃ ሥራውን ለመሥራት በፈቃዱ ውስጥ ተወስኖ የተጠቀሰው የፈቃድ ጊዜ የውሃ ሥራውን ፕሮጀክት ባህሪ መሠረት በማድረግ በተቆጣጣሪው አካል ሊራዘም ይችላል።

፱· *በፈቃድ ያገዙ እና በተቆጣጣሪው አካል መፈጸም ስላለባቸው ተግባራት*

፩· የውሃ ሥራውን ለመሥራት በተወሰነው ወይም በተራዘመው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲሠራ የተፈቀደው ሥራ እንደተጠናቀቀ ወይም ከመጠናቀቁ በፊት ወዲያውኑ እንደነገሩ ሁኔታ ፈቃድ ያገዙ ለተቆጣጣሪው አካል ሥራው መጠናቀቁን ወይም ይጠናቀቃል ተብሎ የሚጠበቀውን ጊዜ በጽሑፍ ማስታወቅ አለበት።

፪· ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ስለሥራው መጠናቀቅ ማስታወቂያ ሲደርሰው ሥራው የተሠራው በፈቃዱ ውስጥ በተመለከቱት ገደቦች እና ሁኔታዎች መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል።

፲· *በውሃ መውረጃዎች ወይም በውሃ ሥራዎች ጣልቃ ስለሚገቡ ሥራዎች*

፩· ከተቆጣጣሪው አካል ፈቃድ ሳይሰጠው ማንኛውም ሰው በውሃ ጉዞ ላይ ችግር የሚያስከትል፣ የውሃ መውረጃን አቅጣጫ የሚቀይር፣ በውሃ መውረጃው የሚፈሰውን የውሃ አፈሳሰስ፣ ፍጥነትንና ኃይል የሚለውጥ ወይም የማንኛውንም የውሃ ነክ ሥራ ትክክለኛ እንቅስቃሴ የሚገታ መሰናክል ሊሰራ ወይም ሊያስቆም አይችልም።

፪· ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የቀረበን ማመልከቻ እንደተቀበለ በእቅዱና በሃሳቡ የታቀፈውን ሥራ ዓላማ፣ እቅዱና ሀሳቡ የሚመለከተው የውሃ መውረጃ በመስጠት ላይ ያለውን ግልጋሎት ሁኔታ የመጠበቅና የመንከባከብ አስፈላጊነትን ግምት ውስጥ በማስገባት ሥራው እንዲሠራ ሊፈቅድ ወይም ለውሃ መውረጃ ደህንነት በቂ ዋስትና ካልተሰጠ በስተቀር ላይፈቅድ ይችላል።

7. The Supervising Body shall cause an entry to be made Register of water abstraction permit in relation to action taken in pursuance of this Article.

## PART THREE
## WATER WORKS PERMIT

7. *Application and Manner of Dealing with them*
   1) An application for the construction, maintenance or alteration of water works shall be made to the Supervising Body.
   2) The application to be submitted pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall contain the design and safety measures along with the detailed study of the water works.
   3) Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article the provision of Article 4(1) (2) (3) and (4) of thise Regulations shall have effect in relation to application for water works construction, re-constructing or altering permits.
8. *Duration and Extension of Permit*
   1) The terms of validity of a water works construction permit shall be fixed by the Supervising Body taking into account the useful life time of the project.
   2) The time limit fixed for the construction of the water works in the water works construction permit may be extended by the Supervising Body taking into account the nature of the water works.
9. *Duties of Permit Holder and Supervising Body on Completing Works*
   1) Upon or immediately before completion of the authorized work within the assigned or extended period, as the case may be, the holder of a permit shall promptLy notify in writing the Supervising Body of the completion or expected completion of the works.
   2) Upon being notified of the completion of works pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the Supervising Body shall ensure the works for compliance with the terms and conditions of the permit.
10. *Works which Interfere with Water Courses or Water Works*
    1) No Person shall construct or install works that cause difficulties for navigation, change the direction of the watercourse affect the flow, speed and belocity of the water flowing in the water cource or hinder the proper operation of any water works, without a permit issued by the Supervising Body.
    2) Upon receipt of the application pursuant to Sub-Article (1) of this Article the Supervising Body having regard to the purposes of the work envisaged in the relevant plan and proposal in so far as it appears to the Supervising Body to be reasonable, to the requirements of existing uses of the water course to which the plan and proposal relates, and to the desirability of protecting and conserving the said water course may clear the plan and proposal, or refuse to clear the plan unless that the works described in the plan and proposal provide sufficient guarantee for the safely of the water course.

## ክፍል አራት
## የውሃ ጥራት ቁጥጥር

፲፩· የታከመ ቆሻሻ ውሃ የመልቀቅ ፈቃድ

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፫/፪/ እና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ድንጋጌዎች መሠረት ማንኛውም ሙያ ነክ ወይም ኢንዱስትሪ ነክ ፍሣሽን ወይም የተበከለ ፍሳሽን ወይም ማንኛውንም መርዛማ፣ ጐጂ ወይም በካይ ነገርን አክሞ በየብስ ውሃ ወይም በከርሰምድር ውሃ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለመልቀቅ የሚያስችል ፈቃድን ለማግኘት ማመልከቻ ለተቆጣጣሪው አካል መቅረብ አለበት።

፪· ተቆጣጣሪው አካል ውሃ ሀብት ውስጥ የታከመ ቆሻሻ የመልቀቅ ፈቃድ ለመስጠት ወይም ለመከልከል ከሌሎች ሁኔታዎች በተጨማሪ የፍሣሽ እና የጅረት ውሃ ጥራት ደረጃን ግምት ውስጥ ያስገባል።

፫· ከዚህ በላይ የተመለከቱት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጾች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ ውስጥ የተደነገጉት ሁኔታዎች የታከመ ቆሻሻ ለመልቀቅ ፈቃድ ለመጠየቅ በሚቀርቡ ማመልከቻዎችም ላይ ተፈጸሚነት ይኖራቸዋል።

፲፪· የታከመ ቆሻሻ ውሃ የሚለቁ ሰዎች ግዴታ

፩· ማንኛውም ውሃን ለኢንዱስትሪ ወይም ብክለትን ሊያስ ከትል ለሚችል ማንኛውም ሥራ ወይም አገልግሎት የሚጠቀም ሰው፤

ሀ) የቆሻሻ ማጣሪያ ዘዴዎችን ወይም መሣሪያዎችን የመትከልና የመጠቀም ግዴታ አለበት፣

ለ) እንዲለቅ የተፈቀደለትን የታከመ ቆሻሻ ዓይነትና መጠን ብቻ መልቀቅ አለበት፣

ሐ) ተቆጣጣሪው አካል በማናቸውም ጊዜ የሚለቀውን የታከመ ቆሻሻ ናሙና እንዲወስድ የመፍቀድ ግዴታ አለበት፣

፪· የዚህን አንቀጽ ድንጋጌዎች ለማስፈፀም ሚኒስቴሩ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፣

፲፫· የታከመ ቆሻሻ የመልቀቅ ፈቃድ እድሳት

፩· የታከመ ቆሻሻ ወደ ውሃ ሀብት የመልቀቅ ፈቃድ በተቆጣጣሪው አካል ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በየሁለት ዓመቱ መታደስ አለበት።

፪· የታከመ ቆሻሻ የመልቀቅ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ከማለቁ ከአንድ ወር በፊት እንዲታደስ ፈቃድ ያገኙ ለተቆጣጣሪው አካል ማመልከት ይኖርበታል።

፫· ተቆጣጣሪው አካል የታከመ ቆሻሻ የመልቀቅ የፈቃድ ማሳደሻ ማመልከቻውን በተቀበለ በአምስት ቀናት ውስጥ በማመልከቻው መሠረት ፈቃዱ ባለበት ሁኔታ መታደሱን ወይም በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ ተደርጐ መታደሱን ወይም ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን ለአመልካቹ በጽሑፍ ያሳውቃል።

፬· ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ንዑስ አንቀጽ መሠረት ተቆጣ ጣሪው አካል ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገ ወይም በፈቃዱ ላይ ማሻሻያዎች ካደረገ ውሳኔው የተመሠረተባ ቸውን ምክንያቶች ጨምሮ በጽሑጽ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት።

፭· ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፫ መሠረት የወሰዳቸውን ማናቸውንም ዓይነት እርም ጃዎች በውሃ የመጠቀም ፈቃድ መዝገብ ውስጥ ይመዘ ግባል።

## PART FOUR
## *WATER QUALITY CONTROL*

11. *Waste Water Discharge Permit*

1) Pursuance to the provisions of Article 13 (2) of the Proclamation and Article 5 of thise Regulations, applications for the direct or indirect discharge of any treated trade effluent or sewerage effluent, or any poisonous, noxious or polluting matter into surface or ground water shall be made to the Supervising Body.

2) In deciding whether to grant or refuse a permit for the discharge of treated waste water into water resources, the Supervising Body shall, among other things, take into consideration effluent and/or stream standards.

3) Subject to the provisions of the preciding sub-articles of this Article, the provisions of Article 4 of thise Regulations shall have effect in relation to applications for treated waste discharge permits.

12. *Obligation of Persons Discharging a treated Waste Water*

1) Any person using water for industry or for any other purposes which may cause pollution shall have an obligation:-

(a) to install and use west treatment method;

(b) to discharge only the type and volume of treated waste permitted;

(c) to allow the Supervising Body to take the treated waste discharge sample at any time;

2) The Ministry many issue directive for the implementation of this Provisions.

13. *Renewal of a Treaty Waste Water Discharge Permits*

1) The Supervising Body shall renew a treated waste water discharge permit very two years starting from the date of its issuance.

2) The permit holder shall apply to the supervising body for the renewal of treated waste water discharge permit not later than one month prior to expiration.

3) Upon receiving an application for the renewal of a treated waste water discharge permit, the Supervising Body shall, within 5 days, notify in writing the applicant that the permit is granted or granted subject to variation, or rejected.

4) The Supervising Body shall notify in writing by stating the reasons why the application is rejected or being varied.

5) The Supervising Body shall cause an entry to be made in the Register of a Treated Waste Water Discharge Permits all actions taken in pursuance to Sub-Article 3 of this Article.

፲፬· <u>የታከመ ቆሻሻ ውሃ የመልቀቅ ፈቃድ መሰረዝ ወይም መታገድ</u>

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፲፯ ለተቆጣጣሪው አካል በተሰጠው ስልጣን የታከመ ቆሻሻ ውሃ የመልቀቅ ፈቃድን በሙሉ ወይም በከፊል ሊያሳግዱ የሚችሉ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ) በፈቃዱ ውስጥ የተጠቀሱ ገደቦችና ሁኔታዎችን አለመጠበቅ ወይም አለማክበር፣

ለ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መተላለፍ፣

፪· ባለፈቃዱ ፈቃዱን ሊያገኝ የቻለው የሀሰት ማስረጃ በመስጠት መሆኑ በተቆጣጣሪው አካል ሲረጋገጥ ፈቃዱ ሊሰርዝ ይችላል።

፫· ተቆጣጣሪው አካል በዚህ አንቀጽ መሠረት የተወሰደ ማንኛውምንም እርምጃ የታከመ ቆሻሻ የመልቀቅ ፈቃድ መዝገብ ውስጥ እንዲመዘገብ ማድረግ አለበት፣

፲፭· <u>የውሃ አቅርቦት ጉድጓዶች የሚቆፈሩበት ቦታ</u>

የውሃ አቅርቦት ጉድጓድ የሚቆፈርበት ቦታና ሁኔታ በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

፲፮· <u>የከርሰ ምድር ውሃ ጥራት ምርመራ</u>

፩· የውሃ አቅርቦት ጉድጓድ ቁፋሮ ተጠናቆ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የጉድጓድ ውሃ ናሙና ሕጋዊ ፈቃድ ላለው ላቦራቶሪ ቀርቦ ለመጠጥነት የሚውል መሆኑ መረጋገጥ አለበት።

፪· የማንኛውም የውሃ አቅርቦት ጉድጓድ ጠረጋ ሥራ ከተካሄደ በኋላ ከጉድጓዱ እድሜ አንጻር ወይም በጠረጋው ሥራ ምክንያት በውሃው ጥራት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ የባክቴሪዎሎጂካልና የኬሚካል ለውጦች መኖራቸውን ወይም አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ሕጋዊ ፈቃድ ባለው ላቦራቶሪ የውሃው ናሙና ቀርቦ ምርመራ መደረግ አለበት።

፲፯· <u>ስለ ውሃ አቅርቦት ጉድጓዶች አያያዝ</u>

፩· የውሃ አቅርቦት ጉድጓድ ውስጥ ማንኛውም በካይ ፍሳሽ ሰርጎ እንዳይገባ በጉድጓዱ ቀፎና በጉድጓዱ መካከል ያለ ክፍት ቦታ መታሸግ አለበት።

፪· ማንኛውም የውሃ ጉድጓድ በቁፋሮና በግንባታ ወቅት በሚያጋጥሙ ችግሮች ሥራው ሳይጠናቀቅ ቢቀር በሰውና በእንስሳት ላይ አደጋ እንዳይደርስና የከርሰ ምድር ውሃ አዘል አካል እንዳይበክል ቆፋሪው ጉድጓዱን በጥንቃቄ መድፈን አለበት።

፲፰· <u>ዘገባ የማቅረብ ግዴታ</u>

በዚህ ደንብ በተገኘ ፈቃድ መሠረት ሥራቸው ስለተጠናቀቀ ወይም ስላልተጠናቀቀ የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ ሥራዎች አፈፃፀም ቆፋሪው ሥራው ከተጠናቀቀ ወይም ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ለተቆጣጣሪው አካል ዘገባ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>ስለ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ስለ ደረጃ አመዳደብ</u>

፲፱· <u>ስለውሃ ሥራዎች ግንባታ</u>

፩· በማንኛውም የውሃ ሥራዎች መስክ መሰማራት የሚፈልግ ባለሙያ ከተቆጣጣሪው አካል የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እስከሌለው ድረስ በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ መሠረት የውሃ ሥራዎች ግንባታ ሥራ ማከናወን አይችልም።

፪· ማንኛውም ሕጋዊ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው የውሃ ሥራዎች ተቋራጭ የውሃ ሥራዎች ግንባታን በተመለከተ ከማንኛውም ሰው ጋር ውል ከመፈጸሙ በፊት የውሃ ሥራው እንዲሠራ በተቆጣጣሪው አካል የተፈቀደ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

14. *Tremination or Suspension of Treated Waste Water Discharge Permits*

1) Based on the power vested on the Supervising Body pursuant to Article 17 of the proclamation, the following shall be reasons for suspension or termination of a treated waste water discharge permit in whole or in part:-

(a) a failure to comply with the terms and conditions prescribed in the permit;

(b) violation of the provisions of Article 12 of thise Regulations.

2) The Supervising Body may terminate a permit when it ascertains that the permit holder has obtained the permit by furnishing false evidence.

3) The Supervising Body shall cause an entry to be made in the Register of waste discharge permit in relation to actions taken in pursuance of this Article.

15. *Sitting for Drilling Water Supply Wells*

The site and the conditions where water supply wells are to be drilled shall be determined by a directive to be issued by the minister.

16. *Ground Water Quality Test*

1. Before the completed water supply well becomes operational the water samples taken from the well shall be ascertained by an authorized laboratory whether it can be used for domestic use.

2) After a rehabilation operation on any water supply well is completed water samples taken from such wells shall be submitted to an authorized laboratory to certain whether changes of bacteriological or chemical nature have or have not occurred in the water either as a result of the age of the well or the rehabilitating operation that has carried out.

17. *Care for Water Supply Wells*

1) To prevent the seepage of surface runoff and sewage into water supply well the space between the well wall and the casing must be sealed.

2) If a water well cannot be completed due to difficulties encountered during drilling and construction, such well must be sealed with care, by the driller, to ensure that people and animals are not exposed to accidents and to prevent pollution of aquifers.

18. *Reporting Obligation*

The driller shall have obligation to submit report to the Supervising Body in accordance with form 10 regarding complete or incomplete water supply wells drilling performance within 30 days after the completion or incompletion thereof.

PART FIVE

*Certification of*

*Professional competence and classification*

19. *Water Works Construction*

1) Subject to Article 11 of the Proclamation, no professional shall engage in the field of water works construction activity unless he obtained a certificate of professional competence issued by the Supervising Body.

2. Any contractor holding a certificate of professional competence shall, before entering into a contract with any body pertaining to water works constructions, first ensure that the Supervising Body has approved that such water works be constructed.

፫· የውሃ ሥራዎች ግንባታ እንዲሠራለት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከውሃ ሥራዎች ተቋራጭ ጋር ውል ከመፈጸሙ በፊት የሥራ ተቋራጩ ድርጅት ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ ያለው መሆኑን እና ባለሙያዎቹም የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

፳· አስፈላጊዎች

፩· ማንኛውም የውሃ ሥራዎች ተቋራጭ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ውስጥ የሚዘረዘሩ መሣሪያዎችና ባለሙያ ያሉት ወይም የእነዚህኑ መሣሪያዎችና ባለሙያዎች አገልግሎት ሊያገኝ የሚችል መሆን አለበት።

፪· የውሃ ሥራዎች ተቋራጭ ለመሆን ያመለከቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት በመመሪያው ተዘርዝሮ የተቀመጠውን መመዘኛ አሟልተው ሲገኙ በሚመጥኑት ደረጃ በተቆጣጣሪው አካል ይመደባሉ።

፳፩ ስለደረጃ አመዳደብ

፩· ተቆጣጣሪው አካል የውሃ ሥራዎች ባለሙያ ለመሆን የቀረበ ማመልከቻን በመገምገም፣

ሀ) አመልካቹ አዋጁ፣ ደንቡ እና መመሪያው የሚጠይቃቸውን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሆኖ ሲያገኘው ደረጃውን በመመደብ አመልካቹ በአለው ደረጃ ለመሥራት የሚችል መሆኑን የሚያረጋግጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩/ሀ/ መሠረት የቀረበ ማመልከቻን ተቆጣጣሪው አካል ሲመረምር አዋጁ፣ ደንቡና መመሪያው የሚጠይቃቸውን ሁኔታዎች የማያሟላ ሆኖ ሲያገኘው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ይከለክላል፣ የከለከለበትንም ምክንያት በጽሑፍ ለአመልካቹ ያሳውቃል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን በየዓመቱ ለተቆጣጣሪው አካል ቀርቦ መታደስ አለበት።

፫· ተቆጣጣሪው አካል የሰጠውን የውሃ ሥራዎች ተቋራጭነት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ተቋራጩ በምስክር ወረቀቱ የተዘረዘሩ ግዴታዎችን ባለመፈፀሙ ምክንያት በማንኛውም ጊዜ ለመሰረዝ ይችላል።

ክፍል ስድስት

ስለአማካሪነት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

፳፪· የአማካሪነት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አስፈላጊነት

በአዋጁ አንቀጽ ፲፱ እንደተደነገገው ማንኛውም ሰው ከተቆጣጣሪው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሳያኖረው ለንግድም ሆነ ለሌላ ዓላማ ከውሃ ሀብት ጥናት፣ ዲዛይን፣ ቁጥጥር እና ግንባታ ጋር የተያያዘ የአማካሪነት አገልግሎት ለመስጠት አይችልም።

፳፫· የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

የአማካሪነት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማውጣት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በሚኒስትሩ በሚወጣ መመሪያ መሠረት የሚጠየቁ አግባብ ያላቸው መረጃዎችን የያዘ ማመልከቻ ለተቆጣጣሪው አካል ማቅረብ አለበት።

3) Any person who wants to have a water works constructed shall, before entering into a contract with a constractor, first ensure that the company has a legal licnese and also the professionals have a certificate of professional competence.

20. *Requirements*

1) Any water works contractor should have or be able to get the service of the equipment and manpower enumerated under the directive to be issued by the Ministry.

2) Persons applying to become water works contractors shall, if found to confirm to the conditions specified under Sub-Article (1) of this Article, be classified under one of the classed on the basis of their capacity by the Supervising body.

21. *Manner of Classification*

1) After the Supervising body examines the appliciation requesting the grant of a certificate of professional competence to undertake water works construction activities, it shall:-

(a) where the applicant is found to meet the requirements of the Proclamation, the Regulations and the directive classify the applicant accordingly and grant him a certificate of professional competence allowing him to operate subject to the conditions of such classifications.

(b) where, during investigation the Supervising Body, finds out that an application submitted under Sub-Article (1) (a) of this Article does not meet the requirements of the Proclamation, the Regulations and the directive it shall reject the application and notify the applicant, in writing, of the rejection and the reasons thereof.

2) A certificate of professional competence issued pursuant to Sub-Article (1) (a) of this Article shall be renewed every year upon presentation to the Supervising Body.

3) The Supervising Body may at any time revoke a certificate of professional competence provided the contractor fails to meet requirements specified in the permit.

PART SIX

*Certificate of Competence for a Consultancy Service*

22. *Necessity of Certificate of Competence for Consultancy Service*

Subject to Article 19 of the Proclamation, no person shall give, whether for commercial purpose or otherwise, without holding a certificate of competence permit issued by the Supervising Body, a consultancy service relating to water resources study, design, supervisions and construction activity water works construction activity pertaining to surface water, or water well drilling or cleaning or relating thereto.

23. *Application for a Competence Certificate*

Any person desiring to have a certificate which enable him to give a consultancy service shall submit an application by specifying the necessary information required under the directive to be issued by the Ministry to the Supervising Body.

፳፬· <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፫ መሠረት ለተቆጣጣሪው አካል ማመልከቻ በደረሰው አስር ቀናት ውስጥ አመልካቹ በመመሪያ የወጣውን ደረጃ ያሟላ መሆኑን በመገምገምና ብቁነቱን በማረጋገጥ የተጠየቀውን የብቃት በማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ወይም ማመልከቻውን ያልተቀበለው ከሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በጽሑፍ ለአመልካቹ ያሳውቃል።

፳፭· <u>ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እድሳት</u>

፩· የአማካሪነት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተቆጣጣሪው አካል በተሰጠ በየአመቱ መታደስ አለበት።

፪· ተቆጣጣሪው አካል የእድሳት ጥያቄ ሲቀርብለት የአማካሪ አገልግሎቱ የሚጠበቅበትን ግዴታ አክብሮና ደረጃውን ጠብቆ የሠራ መሆኑን አረጋግጦ የምስክር ወረቀቱን ያድሳል።

፫· ተቆጣጣሪው አካል የምስክር ወረቀት እድሳት ጥያቄውን ያልተቀበለው ከሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በአስር ቀን ውስጥ በጽሑፍ ለአመልካቹ ያሳውቃል።

፳፮· <u>ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ክፍያ</u>

የአማካሪነት አገልግሎት የምስክር ወረቀት ለማውጣትና ለማሳደስ የሚደረገው ክፍያ በሕግ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል።

፳፯· <u>ስለ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሰረዝ</u>

፩· ተቆጣጣሪው አካል የአማካሪነት ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሚከተሉት ምክንያቶች ባንዱ ሊሰርዝ ይችላል።

ሀ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠው ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) የአማካሪነት አገልግሎቱ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን ባለማክበሩ በተቆጣጣሪው አካል የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በተሰጠው የአንድ ወር የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉድለቶቹን ያላስተካከለ ከሆነ፣

፪· የምስክር ወረቀት የተሰረዘበት ወይም ሥራውን ያቋረጠ ማንኛውም የአማካሪነት አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን ለተቆጣጣሪው አካል መመለስ አለበት።

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>የውሃ ተገልጋዮች ማህበራት</u>

፳፰· <u>ስለ ማህበሮች መቋቋም</u>

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፳፯/፪/ መሠረት በውሃ የመጠቀም ፈቃድ ያላቸው ወይም ከፍቃድ አስፈላጊነት ነጻ የሆኑ ሰዎች የውሃ ተገልጋዮች ማህበር ማቋቋም ይችላሉ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት በሚቋቋሙ የውሃ ተገልጋዮች ማኅበራት ላይ የኅብረት ሥራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር ፩፻፵፯/፲፱፻፺፩ ተፈጻሚ ይሆናል።

፳፱· <u>ስለማኅበራት ምዝገባ</u>

፩· የሚቋቋመው የውሃ ተገልጋዮች ማኅበር የመለስተኛ ወይም ከፍተኛ መስኖ ልማትን የሚመለከት ከሆነ በተቆጣጣሪው አካል መመዝገብ አለበት።

24. *Issuance of a Competence Permit*

The Supervising Body shall issue the certificate applied for in accordance with Article 23 of thise Regulations ten days after receipt of the application after examining and ensuring that the applicant meat the standard issued by the directive or notify the applicant, in writing, of the rejection and the reasons thereof.

25. *Renewal of a Competence Certificate*

1. A Certificate of competence for a consultancy servoce shall be renewed annually starting from the date of its issuance by the Supervising Body.
2. The Supervising Body renew the certificate, upon request, after ascertaining that the performance of the consultancy service is incompliance with the obligations and standard required.
3. If the Supervising Body rejects an application for renewal of a permit, it shall inform same to the applicant within ten days in writing.

26. *Competence Certificate Fee*

Fees for issuance and renewal of competence certificate for a consultancy service shall be as prescribed in Schedule 1 attached to thise Regulations.

27. *Revocation of a Competence Certificate*

1. The Supervising Body may revoke the competence certificate of a consultancy service on any of the following grounds:-
   (a) where the certificate is proved to have been obtained by submitting false evidence,
   (b) where the consultancy service fails, to comply with the provisions of thise Regulations or directives issued for the implementation of thise Regulations and to take corrective measures within one month following a written warning given to it by the Supervising Body.
2. Any consultancy service whose certificate of competence has been revoked or who has ceased operating his activity shall return the permit to the Supervising Body.

PART SEVEN

*WATER USERS COOPERATIVE SOCIETIES*

28. *Formation of Cooperatives*

1. The holders of water use permit pursuant to Article 27(2) of the Proclamation or persons exempted from the requirement of permit may establish a water users cooperative society.
2. Cooperative Societies Proclamation No.147/1998 shall have effect on water users cooperative societies to be established pursuant to Sub-article 1 of this Article.

29. *Registration of a Water Users Co-operative Society*

1. A water users co-operative society established to undertake medium or large sale irrigation shall be registered by the Supervising Body.

፪· የሚቋቋመው የውሃ ተገልጋዮች ማኅበር የአነስተኛ መስኖ ልማትን የሚመለከት ከሆነ በክልሉ ወይም በከተማ መስተዳድሩ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማደራጀት በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል መመዝገብ አለበት ።

፫· በየክልሉ ወይም በከተማ መስተዳድር ደረጃ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማደራጀት በሕግ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የውሃ ተገልጋዮች ማኅበራትን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለተቆጣጣሪው አካል የማስተላለፍ ግዴታ አለባቸው ።

## ክፍል ስምንት
## ስለፈቃድ ክፍያ እና የውሃ ግልጋሎት ዋጋ

፴· ስለፈቃድ አገልግሎት ክፍያ

በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰጡ ፈቃዶችን ለማግኘትና እነዚሁ ፈቃዶች እንዲታደሱ ፣ እንዲሠረዙ ፣ እንዲለወጡ ወይም እንዲተላለፉ ማመልከቻዎች ሲቀርቡ በዚህ ደንብ በሠንጠረዥ ፩ ላይ የተወሰኑ የአገልግሎት ክፍያዎች ለተቆጣጣሪው አካል መከፈል አለባቸው ።

፴፩· ስለ ውሃ አገልግሎት ዋጋ

፩· በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት የውሃ ሀብትን ለማንኛውም ለተፈቀደ ግልጋሎት ለማዋል የውሃ ግልጋሎት ዋጋ ለተቆጣጣሪው አካል መከፈል አለበት ።

፪· በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈሉ የውሃ አገልግሎት ዋጋዎች በተቆጣጣሪው አካል ተተምነው በክፍያ መጠየቂያ በዓመት አንድ ጊዜ ወይም እንደ ሁኔታው ከዚህ ባጠረ ጊዜ ውስጥ መከፈል አለባቸው ።

፫· የውሃ አገልግሎት ዋጋ በዋጋ መጠየቂያ ማስታወቂያ ውስጥ ከሚጠቀሰው ቀን ጀምሮ በ፷ ቀናት ውስጥ መከፈል አለበት ።

፬· የውሃ አገልግሎት ዋጋ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ይወሰናል ።

፴፪· በውሃ ሀብት ውስጥ የታከመ ቆሻሻን ለመልቀቅ ወይም ለመድፋት ስለሚደረግ ክፍያ

፩· በአዋጁ እና በዚህ ደንብ መሠረት በውሃ ሃብት ውስጥ የታከመ ቆሻሻን ለመልቀቅ ወይም ለመድፋት ፈቃድ የተሰጣቸው ሰዎች በሕግ የተወሰነ ክፍያ ለተቆጣጣሪው አካል መክፈል አለባቸው።

፪· በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈሉ ክፍያዎች በየዓመቱ በክፍያ መጠየቂያ ማስታወቂያ ውስጥ ከሚጠቀሰው ቀን ጀምሮ በ፷ ቀናት ውስጥ መከፈል አለባቸው ።

፴፫· ከመንግሥት ፕሮጀክት ለተወሰደ ውሃ ስለሚፈጸሙ ክፍያዎች

፩· በዚህ ደንብ በተሰጠ ፈቃድ መሠረት ከመንግሥት ፕሮጀክት ለተወሰደ ውሃ የሚከፈለው ክፍያ መዋዕለ ወጪውን ተመላሽ በማስደረግ መሠረተ ሃሣብ ላይ ተመሥርቶ በተቆጣጣሪው አካል በሚሰላ ተመን መሠረት ይሆናል ።

፪· በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚከፈሉ ክፍያዎች በየዓመቱ በክፍያ መጠየቂያ ማስታወቂያ ውስጥ ከሚጠቀሰው ቀን ጀምሮ በ፷ ቀናት ውስጥ መከፈል አለባቸው ።

፴፬· የውሃ ግልጋሎት ዋጋን ሳይፈጽሙ መቅረት ስለሚያስከትለው ውጤት

ተቆጣጣሪው አካል የውሃ ግልጋሎት ዋጋ መከፈል ከነበረበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ሥልሣ (፷) ተጨማሪ የችሮታ ቀናት ውስጥ ካልተከፈለ የውሃውን አገልግሎት ማቋረጥ ይችላል ።

2. A water users co-operative society established to undertake small scale irrigation shall be registered by an organ established by law at Regional or City Administration level to organize and register Cooperative Societies.

3. The Regional or City Administration organs that organize and register Cooperative Societies have the obligation to transmit information to the Supervising Body about Water users Co-operative Societies.

## PART EIGHT
## FEES AND CHARGES

30. *Permit Fees*

on an application for a permit under the Proclamation and these Regulations and on an application for the renewal, termination, variation or tansfer of such permits, there shall be payable to the Supervising Body the fees specified in the 1st Schedule to these Regulations.

31. *Charges for use of Water*

1. Water charges shall be paid for any use allowed under the Proclamation and these Regulations to the Supervising Body.
2. Charges payable under this Article shall be assessed and billed for by the Supervising Body once a year, or at such shorter interval, as it is appropriate under the circumstance.
3. Charges for use of water shall be due payable within sixty (60) days from the date appearing on the relevant bill.
4. Charges for use water shall be determined by the Council of Ministers.

32. *Charges for the Discharge of Treated Wastes into Water Resources*

1. Charges specified in the 2nd Schedule to these Regulations shall be paid to the supervising Body by permit holders granted to discharge of release waste into water resources under the proclamation or these Regulations.
2. Charges under this Article shall be billed once a year shall be due and payable within sixty (60) days from the date appearing on the relevant bill.

33. *Charges for the Use of Water from Government Projects*

1. If water is abstracted from a government water works project in respect of a permit granted in accordance with of these Regulations, the charges payable to such water shall be determined by the supervising body based on the principle of cost recovery.
2. Charges under this Article shall be assessed and billed once a year and shall be due and payable within sixty (60) days from the date appearing on the relevant bill.

34. *Effects of Failure to Pay Charges*

The Supervising Body may, stop the supply of water from a government project to the land in respect of which such water is supplied or to the person who is being supplied with water, if charges have not been paid before the expiration of a grace period of sixty (60) days from the date on which such charges had become due and payable.

## ክፍል ዘጠኝ
## ስለ ክርክሮች አወሳሰን

### ፴፭· ስለክርክር አወሳሰን ሥነ-ሥርዓት

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፱/፩/ መሠረት ከፈቃድ ጋር የተያያዙ መብቶችን ወይም ግዴታዎችን በተመለከተ በባለፈቃዶች መካከል ወይም በባለፈቃድና በሦስተኛ ወገኖች መካከል የሚነሱ ማናቸውም ክርክሮች የሚታዩበትና የሚወሰኑበት ሥነ-ሥርዓት እንደሚከተለው ይሆናል ፤

ሀ) አቤት ባዩ የክርክሩን ፍሬ ሃሣብና ማስረጃውን በማመልከቻ ለተቆጣጣሪው አካል ያቀርባል ። ማመልከቻው የአቤት ባዩን ቅሬታና እንዲሰጥለት የሚፈልገውን ውሣኔ መግለጽ አለበት ።

ለ) ተቆጣጣሪው አካል ማመልከቻውን እንደተቀበለ ተከሣሹ መጥሪያና የማመልከቻ ቅጂ እንዲደርሰው ያደርጋል ። ክርክር የሚሰማበትን ጊዜና ቦታም ለሁለቱም ወገኖች ያሳውቃል ።

ሐ) ባለጉዳዮቹ በቀጠሮ ሰዓትና ቦታ ተገኝተው ጉዳያቸውን ለተቆጣጣሪው አካል ያስረዳሉ ፤ ማስረጃዎችንም ያቀርባሉ ። ተቆጣጣሪው አካልም የቀረቡለትን ማስረጃዎች ይመዘግባል ። ተቆጣጣሪው አካል ጉዳዩ በሌላ ጊዜና ቦታ እንደተይ በቀጠሮ ሊያስተላልፍ እንዲሁም በመጀመሪያውም ሆነ ከዚህ በኋላ በተያዘው ቀጠሮ ከባለጉዮቹ አንዱ በሌለበት ጉዳዩን ማየት ሊቀጥል ይችላል ።

መ) ተቆጣጣሪው አካል በጉዳዩ ላይ የሰጠውን ውሣኔ ባለጉዳዮቹ እንዲያውቁት ማድረግና ለእያንዳንዱ ባለጉዳይ የውሣኔውን መዝገብ ግልባጭ መስጠት አለበት ።

ሠ) የዚህ ንዑስ አንቀጽ ሌሎች ድንጋጌዎች እንዲጠበቁ ሆነው በመጀመሪያ ደረጃ የማየት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት በሚታዩ የፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች በተቆጣጣሪው አካል ዘንድ በሚታዩ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

፪· ተቆጣጣሪው አካል የቀረቡለትን ክሶች የክርክሩን ሂደትና የሰጣቸውን ውሣኔዎች መዝገቦ ይይዛል ።

### ፴፮· ስለ ሽምግልና ዳኝነት

፩· በአዋጁ አንቀጽ ፱(፪) ላይ በተደነገገው መሠረት በተቆጣጣሪው አካልና በባለፈቃዱ መካከል የተፈጠረ አለመግባባት በ፷ ተከታታይ ቀናት ውስጥ በጋራ ውይይት ሊፈታ ካልቻለ አንደኛው ወገን ልዩነቶቹ ወይም አለመግባባቶቹ በሽምግልና ዳኞች እንዲታዩለቱ መጠየቅ ይችላል ። ይኸውም፦

ሀ) እያንዳንዱ ወገን ሁለት የግልግል ዳኞች በመምረጥ ለሌላኛው ያሳውቃል ፤

ለ) በሁለቱ ወገኖች የተመረጡት የግልግል ዳኞች ሰብሳቢ የሚሆን ሦስተኛ የግልግል ዳኛ ይመርጣሉ። በስምምነት ሰብሳቢውን መምረጥ ካልቻሉ አፈጻጸሙ በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ በተደነገገው መሠረት ይሆናል ፤

ሐ) የሽምግልና ዳኞች አግባብነት ባላቸው የፌዴራልና የክልል ሕጎች ይመራሉ ፤

መ) ተከራካሪዎቹ በሽምግልና ዳኞች የሚጠየቁትን መረጃዎች የማቅረብና የመተባበር ግዴታ አለባቸው ፤

## PART NINE
## DISPUTE SETTLEMENT

### 35. *Dispute Settlement Procedure*

1. The following procedures shall be applicable in hearing and deciding cases between permit holders, as well as between a permit holder and a third party concerning rights or obligations arising from permits pursuant to Article 9(1) of the Proclamation:–
   (a) the Person complaining shall file with the Supervising Authority a memorandum summarizing the dispute and supporting his allegations. The memorandum shall state nature of the complaint and the relief sought.
   (b) upon receipt of the memorandum, the Supervising Body shall give notice thereof to the adverse party, forwarding a copy of the memorandum reveived, and he shall indicated to both parties the time and place at which the dispute shall be heard.
   (c) At the time and place designated by the Supervising Body the parties shall attend and state their case before him and submit evidence in support thereof. The Supervising Body shall take note of all evidence given. The Supervising Body may adjourn the hearing to any other time and may at the original hearing of any adjournment thereof peroceed in the absence either party.
   (d) The Supervising Body shall inform all parties of his decision regarding the dispute and shall provide each party with a copy of the record of such proceedings.
   (e) The Civil Procedure Code of Ethiopia regulating proceedings before a Court of first instance in civil matters shall apply to proceedings before the Supervising Body without prejudice to the provisions of this Article.
2. The Supervising Body shall keep a record of all disputes; their proceedings and his decisions relating thereto.

### 36. *Arbitration*

1. Subject to Article 9(2) of the Proclamation pending dispute arising between the Supervising Body and the permit holder which could not amicably be settle within 60 consecutive days either party may request to solve the dispute through arbitration. There by:-
   (a) each party shall nominate two arbitrators and inform the other party;
   (b) the arbitrators nominated by the parties shall nominate a third arbitrator as presiding one incase the parties failed to agree accordingly the application shall be as provided in the civil code of Ethiopia;
   (c) the arbitrators shall be governed by the relevant laws of the Federal and Regional government
   (d) the parties shall have the obligation to provide information demanded by the arbitrators and cooperate there with;

ሠ) በሽምግልና ዳኞች የተወሰነበት አካል ውሣኔውን የመቀበል ግዴታ አለበት ሆኖም መብቱ ለሚፈቅድ ድለት ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል ።

፪· የሽምግልና ዳኝነቱ የሚካሄድበትና ውሳኔ የሚሰጥበት ቦታ የተቆጣጣሪው አካል ዋና መ/ቤት በሚገኝበት ከተማ ይሆናል ።

፫· ለሽምግልና ዳኞች አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ግራ ቀኞቹ በጋራ የመሸፈን ግዴታ አለባቸው ፣

፬· በዚህ አንቀጽ ያልተሸፈኑ ጉዳዮችን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ እና የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ።

## ክፍል አሥር
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፴፯· መረጃዎችን የመጠየቅ ሥልጣን

ተቆጣጣሪው አካል ከዚህ በታች የተመለከቱት ሰዎች በያዙት ፈቃድ መሠረት ወይም ሕጉ በሚያዘው መሠረት ስለሚያካሄዱት ተግባር መረጃ እንዲሰጡት በዝርዝር ሊጠይቅ ይችላል ።

እነዚህም ፦

ሀ) በዚህ ደንብ ክፍል ፪ ፣ ፫፣ ፬፣ ፭ ፣ ፮ እና ፯ ድንጋጌዎች መሠረት ፈቃድ የያዘ ሰው ወይም

ለ) በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ መሠረት የውሃ ጉድጓድ የሚቆፍር ወይም ከዚሁ ጉድጓድ ውሃ የሚወስድ ማንኛውም ሰው ።

### ፴፰· የመግባት ፣ የመመርመርና ናሙናዎችን የመውሰድ ሥልጣን

ተቆጣጣሪው አካል የፈቀደለት ወይም ሥልጣን የሰጠው ማንኛውም ሰው ሥልጣኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በመያዝ በማንኛውም መሬት ወይም ቦታ ተገኝቶ፣

ሀ) የአዋጁና የደንቡ ድንጋጌዎች እንደዚሁም በተሰጠው ፈቃድ ውስጥ የተዘረዘሩት ገደቦችና ሁኔታዎች የተጠበቁ መሆኑን ለመከታተል ፣

ለ) የውሃ ጥራት ሁኔታዎችን ለመመርመርና ለማጥናት ፣

ሐ) ለአዋጁና ለዚህ ደንብ ዓላማዎች አስፈላጊ የሆኑ ማንኛቸውንም መሣሪያዎች ለመትከል ለመጠገን ለማንበብ ወይም ለመፈተሽ ፣

መ) በውሃ ጉድጓድ ውስጥ ተቆፍረው የወጡትን ነገሮች ለመመርመር ፣

ሠ) በማንኛውም ዓይነት ዘዴ የተወሰደውን ወይም ሊወሰድ የሚችለውን የውሃ መጠን ለማረጋገጥ ፣

ረ) በዚህ ደንብ መሠረት የተያዙ መዝገቦችን ለመመርመር ፣

ሰ) የማንኛውንም ውሃ ናሙና ወይም ፍሳሽ ወይም የውሃ ጥራትን ሊነካ ይችላል ብሎ የሚገምተውን ማንኛውንም ነገር ለመውሰድ ፣ ሥልጣን ይኖረዋል።

### ፴፱· ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከመጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ መጋቢት ፳ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

(e) the party against whose a decision is given shall have the obligation to be bound thereby; however a party disfavored shall have the right to appeal to the court having jurisdication.

2. The sit of the arbitration shall be in the town where the Head Quart of the Supervising Body is located.
3. The parties shall have the obligation to cover the expenses necessary to the arbitrators.
4. The provisions of the Ethiopian Civil and Civil Procedure Code shall be applicable on matters; which are not covered by this Article.

## *PART TEN*
## *MISCELLANEOUS PROVISIONS*

### 37. *Power to Require Information*

The Supervising Body may require:-

(a) the holder of a permit under part 2, 3, 4, 5 and 6

(b) any person who digs a well or abstracts water there from pursuant to Article 12 of the Proclamation to give such information as to the activities performed under a permit or the authority of the Proclamation as it may be specified in the request.

### 38 *Power of Entry, Inspection and Taking of Samples*

Any person authorized by the Supervising Body shall on producing authenticated document showing his authority, be entitled to enter upon any land:

(a) to monitor compliance with the provisions of the Proclamation and these Regulations, and with any conditions subject to which a permit has been granted;

(b) to inspect and study conditions relating to the quality of water;

(c) to install, maintain, read or test any instrument installed for the purposes of the Proclamation and thise Regulations;

(d) to examine substances obtained during a water well drilling;

(e) to ascertain the quantity of water abstracted or capable of being abstracted by means of of any method;

(f) to examine records kept for the purpose of thise Regulations;

(g) to take a sample of any water or effluent or other substance which may appear to him as being cpable of affecting the quality of water.

### 39. *Effective Date*

Thise Regulations shall enter into force as of 29th day of March, 2005

Done at Addis Ababa, this 29th day of March 2005

*MELES ZENAWI*
*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

## ሠንጠረዥ ፩
## የፈቃድ አገልግሎት ክፍያ ተመን

| ተ.ቁ. | የፈቃድ አገልግሎት | ተመን |
|---|---|---|
| 1 | የውሃ ባለሙያ የምሥክር ወረቀት ለማውጣት | 60·00 |
| 2 | የውሃ ኮንስትራክሽን ባለሙያ የምሥክር ወረቀት ለማውጣት | 67·00 |
| 3 | የዲዛይን የረጅም ጊዜ ባለልምድ ባለሙያ የምሥክር ወረቀት ለማውጣት | 85·00 |
| 4 | የአማካሪነት አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ለማውጣት | 151·00 |
| 5 | የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ወይም ጠረጋ ሥራ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት | 72·00 |
| 6 | የውሃ ሥራዎች ተቋራጭነት የብቃት ምሥክር ወረቀት ለማውጣት | 162·00 |
| 7 | የታከመ ቆሻሻ ወደ ውሃ አካል ለመልቀቅ ፈቃድ ለማውጣት | 81·00 |
| 8 | የውሃ ለመጠቀም ፈቃድ ለማውጣት | 87·00 |
| 9 | የውሃ ሥራዎችን ለመሥራት ወይም ለመለወጥ | 94·00 |
| 10 | ጣልቃ ገብ ሥራዎችን መሥራት ወይም ለመለወጥ | 88·00 |
| 11 | በውሃ ለመጠቀም የተሰጠ ፈቃድን ለማሠረዝ ፡ ለማስተላለፍ ወይም ለመለወጥ | 55·00 |
| 12 | የውሃ ሥራዎችን ለመሥራት ወይም ለመለወጥ የተሰጠ ፈቃድን ለማራዘም ፡ ለማሠረዝ ፡ ለማስተላለፍ ወይም ለመለወጥ | 54·00 |
| 13 | ቆሻሻን ወደ ውሃ አካል ለመልቀቅ የተሰጠ ፈቃድን ለመለወጥ ወይም ለማሠረዝ | 41·00 |
| 14 | የውሃ ተጠቃሚዎች ማኅበራት ዕውቅና ለማግኘት | 54·00 |
| 15 | የውሃ ባለሙያ የምስክር ወረቀት ለማደስ | 44·00 |
| 16 | የውሃ ኮንስትራክሽን ባለሙያ የምሥክር ወረቀት ለማደስ | 52·00 |
| 17 | የዲዛይን የረጅም ጊዜ ለልምድ ባለሙያ የምሥክር ወረቀት ለማደስ | 74·00 |
| 18 | የአማካሪነት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ለማደስ | 91·00 |
| 19 | የውሃ ጉድጓድ ቁፋሮ እና ወይም ጠረጋ ሥራ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ለማደስ | 63·00 |
| 20 | የውሃ ሥራዎች ተቋራጭነት የብቃት የምሥክር ወረቀት ለማደስ | 102·00 |
| 21 | የታከመ ቆሻሻ ወደ ውሃ አካል ለመልቀቅ የተሰጠ ፈቃድን ለማደስ | 74·00 |

## *SCHEDULE*
## *FEES FOR PERMITS*

| *No.* | *Type of Permits* | *Amount In Birr* |
|---|---|---|
| *1* | *Certification of Professional Competence for Water Engineering* | *60.00* |
| *2* | *Certificate of Professional Comptence for Water Works Construction* | *67.00* |
| *3* | *Certification of Highly Experienced Professional Designer* | *85.00* |
| *4* | *Consultancy Services Competence Certificate* | *151.00* |
| *5* | *Certificate of Professional Competence for Water Well Drilling and/or Rehabilitation Permit* | *72.00* |
| *6* | *Water Works Contractors Permit* | *162.00* |
| *7.* | *Waste Discharge Permit* | *81.00* |
| *8.* | *Water Use Permit* | *87.00* |
| *9.* | *Water Works Construction or Alteration Permit* | *94.00* |
| *10.* | *To Open File for Works which Interfere with Inland Waters or Water Works* | *88.00* |
| *11.* | *Water Use Permit Cancellation, Transfer or alteration Permit* | *55.00* |
| *12.* | *Water Works Construction or Alteration Permit Extension, Cancellation, Transfer or Alteration* | *54.00* |
| *13.* | *Waste Discharge Permit Alteration or Cancellation* | *41.00* |
| *14.* | *Water Users Association Certifcation* | *54.00* |
| *15.* | *Renewal of Certificate of Professional Competence for Water Engineering* | *44.00* |
| *16* | *Certificate of Professional Competence for Water Works Renewal* | *52.00* |
| *17.* | *Highly Experienced Professional Designer Certificate Renewal* | *74.00* |
| *18* | *Consultancy Servies Competence Certificate Rrenewal* | *91.00* |
| *19* | *Certificate of Professional Competence for Water Well Drilling and/or Rehabilitation Renewal* | *63.00* |
| *20* | *Water Works Contractors Permit Renewal* | *102.00* |
| *21* | *Waste Discharge Permit Renewal* | *74.00* |

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት